**የልማት ጥናቶች መልከዓ ምድር፤ ማንንም ወደ ኋላ ያለ መተው**

ሎጋን ኮክሬን እና አሌክ ቶርንቶን

ይህንን ጽሑፍ ለመጥቀስ የሚከተለውን ይጠቀሙ፤ Logan Cochrane & Alec Thornton (2017): The Geography of Development Studies: Leaving No One Behind, Forum for Development Studies, DOI: 10.1080/08039410.2017.1345786

በሚከተለው ድረ-ገጽም ይገኛል፤ http://dx.doi.org/10.1080/08039410.2017.1345786

# የልማት ጥናቶች መልከዓ ምድር፤ ማንንም ወደ ኋላ ያለ መተው

ሎጋን ኮክሬን[a] እና አሌክ ቶርንቶን[b,c]

*[a] ካርልተን ዩኒቨርስቲ፣ ካናዳ [b] ፊዚካል ኢንቫይሮመንታል ኤንድ ማቲማቲካል ሳይንስስ፣ ዩ.ኤን.አስ.ደብሊው ካንቤራ፣ አውስትራሊያ፤ [c] ስኩል ኦቭ ቱሪዝም ኤንድ ሆስፒታሊቲ፣ ፋኩሊቲ ኦቭ ማኔጅመንት ዩኒቨርስቲ ኦቭ ጆሃንስበርግ፣ ሳውዝ አፍሪካ*

**አጠቃሎ**

*የምዕተ-ዓመት የልማት ግቦች በቅነሳ ላይ አተኩረው የነበር ሲሆን፣ የዘላቂ ልማት ግቦች ላይ ግን በጉልህ ማንንም ወደ ኋላ ያለ መተውን የሚያመላክቱ አዲስ ግቦችን አካትቷል፡፡ ይህ ማብራሪያ በልማት ጥናት ምርምር ውስጥ ያለውን መልከዓ ምድራዊ ቀዳሚነት እና አለመካተት እንዲሁም መንስዔዎቹን ይዳስሳል፡፡ አንድም ሰው ወደ ኋላ እንዳይተው በምርምር፣ እንዲሁም በተመራማሪ ማኅበረሰብ ላይ ልዕለ-ለውጥ ሊከናወን ያስፈልጋል፡፡ ተደራሽ እና ሁሉን አቀፍ የሆነ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደትን ለመደገፍ የሚያስችል ማስረጃን ማቅረብ፣ ተመራማሪው ማኅበረሰብ ክፍተቶችን በሚሞላ መንገድ በተሻለ አካታች የሆነውን የዘላቂ ልማት ግብ ለመደገፍ እንዲቻላቸው የሚረዳ አፍላቂነት እና የፈጠራ ችሎታ በተሞላበት መልኩ ያለውን ነባራዊ ያለማጠቃለል ሁኔታ ማስላት አስፈላጊ ነው፡፡ እንደ ተመራማሪ ማኅበረሰብ ይህንን ጥሪ በቁም ነገር የምንወስደው ከሆነ፣ የአስተሳሰብ አመራር እና ማስረጃ ምርምራችንንም ልምዳችንንም ወደ ልዕለ-ለውጥ የሚያደርሱ መነሻዎች ይሆኑልናል፡፡*

**ቁልፍ ቃላት፡-** *ዘላቂ የልማት ግቦች፣ የልማት ጥናቶች፣ ዓለም-አቀፍ ልማት፣ የልማት መልከዓ-ምድር*

## መግቢያ

ዘላቂ የልማት ግቦች በልማት አካሄድ ውስጥ እጅግ ጠቃሚ ለውጥን ያመላክታሉ፡፡ በቅነሳ ላይ ከሚያተኩሩት ከምዕተ-ዓመቱ የልማት ግቦች በተለየ፣ ዘላቂ የልማት ግቦች ፈጽሞ በማስቀረት ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ ‘አንድንም ሰው ወደ ኋላ ላለ መተዉ’ ብርቱ ሉላዊ መሰጠት ይታያል (UN, 2016; UNDP, 2016)፡፡ ይህ አጀንዳ የሚያስመሰግን እና ፈታኝ ነው፡፡ እኒህን ጽኑ መሻት የሚታይባቸው ግቦች እውን ወደ ማድረግ ለመጓዝ ተጨባጭ የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት እና ጥረት ያስፈልጋል፡፡ በ2017 የወጣው ፎረም ፎር ዲቨሎፕመንት ስተዲስ ልዩ እትም በዘላቂ የልማት ግቦች ዓውድ (Scholte and Soderbaum, 2017) ውስጥ ምን አዲስ እና የተለየ ነገር እንዳለ ሲያመላክት፣ ከመረጃ(Jerven, 2017)፣ ፍትሕ (Bigsten, 2017) እና የመፈራረስ አደጋ ከተጋረጠባቸው ሀገራት (Boas, 2017) ጋር የተያያዙ ጠቃሚ ጉዳዮችን አካትቷል፡፡ ነገር ግን፣ ተመራማሪዎች እያጋጠማቸው ካሉ አዳጋች ሁኔታዎች ውስጥ ትልቁ፤ እርሱውም የልማት ጥናቶች ምርምር መጠን እና አስተዋጾ የሚያደርጉት ተመራማሪዎች ማኅበረሰብ ‘ማንንም ወደ ኋላ ላለመተው’ የተተለመውን አጀንዳ ለመደገፍ ተገቢው ቦታ ላይ መሆን አለመሆኑን እንዳልዳሰሰ እናምናለን፡፡ የልማት ጥናቶች ምርምር መልከዓ-ምድራዊ የዓለም ሀገራትን የማስቀደም እና የመተው ባህሪ እንዳላቸው፣ ይህም ለበለጠ ኢ-እኩልነት እንደሚዳርግ አንስተን እንሞግታለን፡፡ ይህም የግለሰቦች ምርጫ ሳይሆን፣ የተማራማሪዎች ማኅበረሰብ የጋራ ውሳኔ ተጽዕኖ እንደ ሆነ እናስባለን፡፡ ሁኔታው

ምርምር የሚካሄድበትን ጉዳይ፣ የት እና በምን ያህል ድግግሞሽም ሊደረግ እንደሚችል ይወስናል፡፡ ስለዚህ፣ ተመራማሪዎች የምርምር ርዕሶቻቸውን እንዲመርጡ የሚኮረኩራቸው ምን እንደ ሆነ፣ ለምን እንደ ሆነ እና ምን ዓይነት ችግሮችንም እንደሚያስከትል እንመለከታለን፡፡ የተመራማሪዎች ማኅበረሰብ ተግባራቶቻችን አካታች እና ተደራሽ ፖሊሲ እና ተግባርን የምዕተ-ዓመቱ የልማት ግቦች ያተኮሩበትን ቅነሳ እንዲሁም ዘላቂ የልማት ግቦች ያተኮሩበትን ማስወገድ እንዲደግፉ ለማስቻል፣ ተጨባጭ ለውጥ እንደሚያስፈልግ እናመላክታለን፡፡

ዘላቂ የልማት ግቦችን እና 'አንድንም ሰው ወደ ኋላ ያለ መተዉ' አጀንዳ የምንደግፍ ቢሆንም፣ ዘላቂ የልማት ግቦች የራሳቸውን አዳጋች ሁኔታ እንዳላቸው እውቅና እንሰጣለን፡፡ 17ቱ ግቦች፣ 169ኙ ዓላማዎች እና 230 መመዘኛዎች የምዕተ-ዓመቱ የልማት ግቦች የነበራቸውን ዓይነት የውሳኔ አሰጣጥ ሊደግሙ ይችላሉ፡፡ እንደ የሳይንስ ዓለም-አቀፍ ካውንስል እና ዓለም-አቀፍ የማኅበራዊ ሳይንስ ካውንስል አገላለጽ ከግቦቹ አንድ ሦስተኛ ያነሱት ብቻ ናቸው በሚገባ የተተነተኑት፣ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በይበልጥ ተለይተው በተነጠሉ ጉዳዮች ላይ ማተኮር የሚኖርባቸው ሲሆን፣ 50 የሚያህሉት ደግሞ ተጨማሪ ሥራ ያስፈልጋቸዋል (ICSU and ISSC, 2015)፡፡ የአመላካቾች እና መመዘኛዎች መዋቅ/ኢንዲኬተርስ ኤንድ ሞኒተሪንግ ፍሬምወርክ የተሻለ ግንዛቤን ያስገኘ (UN SDSN, 2015) ቢሆንም፣ መመዘኛዎቹ ግልጽ ግንዛቤ የሚጎድላቸው ሲሆን፣ አብዛኛዎቹ እንደ ምዕተ-ዓመቱ የልማት ግቦች ሁሉ በቅነሳ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው (Hak et al., 2016)፡፡ ወጪ ቆጣቢነት በቀዳሚነት መቀመጡ ከሰብዓዊ መብት፣ ተደራሽነት እና ትልልቅ ጉድለቶች ይልቅ ለገንዘብ ዋጋ መስጠትን ሊያስቀድም ይችላል (Cochrane and Thornton, 2016; Eyben et al., 2015)፡፡ ነገር ግን፣ ይህ የጥናት ጽሑፍ በዘላቂ ልማት ግቦች ዝርዝር ላይ የሚያተኩር አይደለም፡፡ በአንጻሩ፣ በዘላቂ ልማት ግቦች አንድንም ሰው ወደ ኋላ ያለ መተዉ መሻት እና ራዕይ ላይ በማተኮር፣ በዚያ ዙሪያ የልማት ጥናቶች ምርምር የላቸውን አስተዋጾ ይዳስሳል፡፡

የልማት ገንዘብ አቅርቦት ሁሉንም ጊዜ በጉድለት ላይ ተመስርቶ የማይሰጥ ሲሆን፣ እርዳታ ደግሞ በፖለቲካዊና ስትራተጂያዊ ፍላጎቶች፣ እንዲሁም በታሪካዊ እና የንግድ ግንኙነቶች የሚወሰን ነው (Alesina and Dollar, 2000; Barro and Lee, 2005; Berthelemy, 2006; De Mesquita and Smith, 2009; Dollar and Levin, 2006)፡፡ የዚህም ውጤት ውሳኔዎች በሌሎች ምክንያቶች ሊወሰኑ ስለሚችል ትልቅ እጦት የገጠማቸው ግለሰቦች፣ ሀገራት እንዲሁም ክልሎች ቸል እንዲባሉ ወይም ከተገቢው ያነሰ የገንዘብ አቅርቦት እንዲደረግባቸው አስተዋጾ ያደርጋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ፣ በምርምሩ ዓለምም ለጋሾች ጉድለት  አሳሳቢ በመሆኑ ላይ ሳይመሰረቱ የገንዘብ አቅርቦት ሊያካሂዱ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ በአየር ንብረት ለውጥ ላይ የሚደረግን ጥናት እንመልከት፡፡ ዐብይ ለጋሾች ለሚደርሰው ጥፋት ተገቢውን መቋቋም የሚያስችል ምላሽ ለመስጠት አቅም ለሌላቸው ሀገራት ቅድሚያ ከመስጠት ይልቅ ውሳኔያቸውን ባላቸው ታሪካዊ እና ፖለቲካዊ ትይይዝ ላይ ሊመሰርቱ ይችላሉ (Hendrix, 2017)፡፡ እንደ ዓለም ባንክ አከፋፈል ሁኔታ (2016)፣ በዩናይትድ ኪንግደም የገንዘብ አቅርቦት የሚደረግለት ክላይመት ኤንድ ዴቭሎፐመንት ኖውሌጅ ኔትወርክ ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ይልቅ መካከለኛ ገቢ ላላቸው አያሌ ሀገራት ቅድሚያ ሰጥቷል (CDKN, 2016)፡፡ በካናዳው ዓለም-አቀፍ የልማት እ ምርምር ማዕከል ስር የሚተዳደረው ሪሰርች ኢኒሺዬቲቭ ኢን አፍሪካ ኤንድ ኤዥያም እንዲሁ ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ይልቅ መካከለኛ ገቢ ላላቸው ሀገራት ቅድሚያ ሰጥቷል (CARIAA, 2016)፡፡ እነዚህ ለጋሾች ሁሉም ምርምር የት እንደሚካሄድ ባይወስኑም፣ ተመራማሪዎች የትኛው ስፍራ ቢሆኑ የተሻለ ዕድል እንደሚኖራቸው (እንደማይኖራቸውም ጭምር) በተመለከተ ተጽዕኖ ያሳድራሉ፡፡ የዚህ ቸልታ እና ዝቅተኛ የሀነ የገንዘብ አቅርቦት ውጤትም እጅግ ዝቅተኛ የመቋቋም አቅም እና ከፍተኛ ተጋላጭነት ያላቸው ሀገራት፣ ከሌሎች ሀገራት ጋር ሲነጻጸር እንዲተዉ ወይም ወደ ኋላ እንዲቀሩ ያደርጋል፡፡

የጥናት እና ምርምርን ጨምሮ የልማት የገንዘብ አቅርቦት ፖለቲካዊ ተፈጥሮ ከልማት ጥናት እና ተመራማሪዎች ቁጥጥር እና ተጽዕኖ ውጪ ነው፡፡ በምርምር የገንዘብ አቅርቦት ቸል የተባሉት ሀገራት የመተዋቸው መጠን ምን ያህል በምርምር ላይ ተንጸባርቋል? ቻምበርስ (1981) በ'ተቀናጀ የገጠር ልማት ጉብኝት' ውስጥ የልማት ባለሙያዎች ከድህነት እና ድሆች ጋር የተቻለው ዝቅተኛ ግንኙነት የሚኖራቸውን ሁኔታ በተመለከተ ስድስት መሠረቶችን እንደሚከተለው አስቀምጧል፡- መገኛ፣ ፕሮጀክት፣ ሰው፣ ደረቅ-ወቅት፣ ዲፕሎማሲያዊ እንዲሁም ሙያዊ፡፡ እንዲህ ያሉት ከግላዊ አመለካከለት የሚመነጩ አድልኦዎች የሚኖረውን አጭር የጉብኝት ቆይታ የተሳሳተ መረጃ የሚገኝበት እና የገጠሩን የኑሮ እውነታ 'ከሚገባው ባነሰ' የሚመለከት ሲያደርገው፣ የልማት ሠራተኞችም በአሉታዊ መልኩ 'የልማት ጎብኚ' ተደረገው ይፈረጃሉ (Chambers, 1981, p. 1)፡፡ ራሱን እንደ አሉታዊ ምሳሌ በማቅረብ፣ ወጣት ተመራማሪ

ሆኖ ሳለ፣ በሥራ ባልደረቦቹ ዘንድ አዳጊ ዝናን የማስገኘት እድል ስለ ነበረው ወደ አንድ የምርምር ጣቢያ ማመዘኑን ይናገራል (‘የፕሮጀክት አድልዎ’) (Chambers 2006, p. 20)፡፡ ከታች በዝርዝር እንዳሰፈርነው፣ ይህ በአንድ ምሁራዊ ምህዳር ወይም ወይይት (ሊጋሽ አካላትን፣ የፖሊሲ ቀረጻን እንዲሁም ሌሎች አቅርቦቶች በተገቢው ቦታ ያለ ማረፋቸውን ጨምሮ) ውስጥ ከተገቢው በላይ የመወከልን ሁኔታ ሊያስከትል ይችላል ወይም ያስከትላል፡፡

ዘላቂ የልማት ግቦች የልማት ትግበራዎችን ልዕለ ለውጥ የመፈለጋቸውን ያህል፣ እኛ እንደ ተመራማሪነታችን የልማት አጥኚ ማኅበረሰቡ ለኢ-እኩልነት አስተዋጾ ሊያደርግባቸው የሚችላቸውን መንገዶች በጥንቃቄ አሰላስሎ መፍትሔ መፈለግ ይኖርበታል፣ ያ ካልሆነ እንደ ማኅበረሰብ የምንመርጣቸው ምርጫዎች ዘላቂ የልማት ግቦች ሊያስቀሩ የሚሹትን ያለማካተትን ይብስ ስር ያሰድዱታል፡፡ ይህ የሙግት ጽሑፍ የልማት ተግባር ሊከወንበት የተገባ ስፍራ ‘የት’ እንደ ሆነ ማመላከት አይደለም (ለምሳሌ፡- የዓለም-አቀፍ ልማት ፍሰት እና ክንውን አካሄድ)፡፡ በአንጻሩ፣ የልማት ጥናትና ምርምር ባተኮረበት እና ከዚያው ጋር ተያይዞ ቸል በተባለበት መካከል ያለውን ምሁራዊ የ‘ስፍራ’ ክፍተት ማመላከት ላይ ያተኩራል፡፡ በጉዳዩ ላይ ጠቃሚ ማስረጃን ለማካተት ሲባል፣ በልማቱ ዘርፍ የረዥም ጊዜ ቆይታ ካላቸው አንዱ ከሆነው ከጆርናል ኦቭ ዴቨሎፐመንት ስተዲስ (ጄ.ዲ.ኤስ) ውስጥ የ50 ዓመታት (1964–2014) ሕትመቶችን መርጠን ተመልክተናል፡፡ ሀገራትን ለመፈለግና በዓመታዊ መልኩ በሰንጠረዥ ለማስቀመጥ የጄ.ዲ.ኤስን የሕትመት ውጤቶች ተጠቅመናል፡፡ የዚህ አቀራረብ ቀዳሚ ገደቦች ቁልፍ ቃላቱ የሚገኙበትን ዐውድ፣ እንዲሁም በእያንዳንዱ ጽሑፍ ውስጥ ያለውን ድግግሞሽ ለማስላት ያለመቻሉ ነው፡፡ ውጤቶቹን በምርምር ዓለም ውስጥ ያለውን መልከዓ-ምድራዊ ያለ መመጣጠን ለማመላከት እና የተማራማሪዎች ማኅበረሰቡ ከጋራ ምርጫዎች የመጡ ያለመመጣጠን ሁኔታዎችን ለመፍታት በንቃት እንዲሳተፉ የሚያስችል ውይይት ለመፍጠር እንደሚጠቅሙ በማመን አስፍረናቸዋል፡፡ ይህ ሌሎች እንዳደረጉት፣ ለምሳሌ (Alesina and Dollar, 2000; Hendrix, 2017) በዘርፉ ላይ የተደረገ ስልታዊ ምዘና አይደለም፡፡ በአንጻሩ፣ ዓለም-አቀፍ የልማት ጥናት ተመራማሪዎች ማኅበረሰቡ የጋራ ሥራችን እንዴት ባለ መንገድ አንድንም ሰው ወደ ኋላ ያለመተውን ማስፈጸም እንደሚችል በተመለከተ ስለ መልከዓ-ምድራዊ ተካታችነት እና ቀሪነት ውይይት ለመፍጠር የታለመ ነው፡፡

**የልማት ጥናት ምርምሮች እና ማንንም ሰው ወደ ኋላ ያለ መተዉ**

በልማት ጥናቶች መልከዓ-ምድር ላይ የሚገኙ ጽሑፎች እንዳሳዩት (ለምሳሌ፡- Alesina and Dollar, 2000; Hammett and Gough, 2016; Hendrix, 2017)፣ በልማት ምርምር መልከዓ-ምድሩ ላይ ኢ-እኩልነት የሚታይ ሲሆን፣ የእኛም ምዘና ያንኑ ያመላክታል (ሰንጠረዥ 1)፡፡ በልማት ጥናት ምርምር ዘርፍ ያለው መልከዓ-ምድራዊ እውቀት ላይ ተጽዕኖ ያላቸው አራት ምክንያቶችን ለይተን አውጥተናል፤ እነርሱም ተደራሽነት፣ ሕዝብ፣ ቋንቋ እና ግንኙነቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ምክንያቶች ከዘላቂ የልማት ግብ ማንንም ያለ መተዉ አጀንዳ አንጻር ጠቃሚ ውይይትን ለማነሳሳት የታለሙ ቢሆንም፣ አንዱ ምክንያት ለብቻው፣ ወይም አንድ የምክንያቶች ስብስብ የልማት ጥናት ምርምሮች የት፣ ለምን እና መቼ እንደሚካሄዱ ይገልጻሉ ማለት እንዳልሆነ እናስባለን፡፡

| በተደጋጋሚ የተጠቀሱ | # | ጥቂት ጊዜ የተጠቀሱ[a] | # (በቡድን ቢዘረዘሩ አማካይ) |
|---|---|---|---|
| ሕንድ | 1248 | ቡታን | 8 |
| ቻይና | 661 | በማደግ ላይ የሚገኙ ትንንሽ ግዛቶች (35)[b] | 396(11) |
| ብራዚል | 586 | የስሎቫኪያ ሪፐብሊክ | 11 |
| ሜክሲኮ | 572 | ብሩኔ ዳሬሰላም | 12 |
| ኬንያ | 484 | ድህረ-ሶቭየት ሀገራት (14)[c] | 195 (14) |
| ኢንዶኔዥያ | 443 | ሱሪኔም | 15 |
| ፊሊፒንስ | 395 | የኮንጎ ሪፐብሊክ | 16 |
| ፓኪስታን | 389 | ጅቡቲ | 16 |
| ጋና | 386 | ኢኳቶሪያል ጊኒ | 19 |
| ታንዛኒያ | 383 | ሰሜን ኮሪያ | 24 |
| ቺሊ | 369 | ቤሊዝ | 25 |
| ባንግላዴሽ | 359 | የባህረሰላጤ የትብብር ሀገራት (5)[d] | 130 (26) |
| ደቡብ አፍሪካ | 357 | አልባኒያ | 29 |
| ናይጄሪያ | 346 | ኤርት | 36 |
| ፔሩ | 317 | የመን | 36 |
| አርጀንቲና | 315 | የመካከለኛው አፍሪካ ሪፐብሊክ | 37 |

ሰንጠረዥ ፩፡ ሀገሮች የተጠቀሱበት ድግግሞሽ፣ ከ1964-2014 (ኦ.ኢ.ሲ.ዲን ሳያካትት)

በሰንጠረዥ ፩ የተቀመጠውን መረጃ ያቀረብንበት ዓላማ መልከዓ-ምድራዊ ቅድሚያዎችን እና ያለማካተቶችን በሚያሳይ መልኩ በልማት ጥናት ምርምር ውስጥ ያለውን ጠቃሚ የመልከዓ-ምራዊ ማዕከላዊነት መዳረሻ ማሳየት ነው፡፡ ይህ ውጤት ለረዥም ጊዜ በተጽዕኖ አምጪነት የዘለቀው የጥናትና ምርምር ሕትመት ላይ የተገኘን ውጤት የሚያንጸባርቅ ቢሆንም፣ የተጠቀምነው ሕትመት አንድ ብቻ መሆኑ ውጤቱን ሁሉን አቀፍ አያደርገውም፡፡ እንዲያም ቢሆን፣ ያሉትን አዳጋች ሁኔታዎች ለመግለጥ እና በተለይም በምርምር ማኅበረሰቡ ማንንም ወደ ኋላ ያለመተውን ዓላማ ወደ ፊት ለማስኳዝ ደጋፊ ሚና ይጫወት ዘንድ፣ ተጨባጭ የሆነ አሰላስሎትን ለማበረታታት ውጤቶቹን ተጠቅመናል፡፡

**ተደራሽነት**

ተደራሽነት ሁለቱንም፣ ምርምር ማካሄድ ችሎታን (ለምሳሌ ከውጪ የሚመጡ ተመራማሪዎች ፖለቲካዊ ፈቃደኝነት) እና ደህንነትን (ለምሳሌ ተመራማሪዎች ደህንነቱ በተጠበቀ ስፍራ ምርምር ማካሄድ መቻላቸው እና ያንን ለማድረግ ፈቃድ ማግኘታቸው) ያጠቃልላል፡፡ ስማቸው ከልማት ምርምር አኳያ በጥቂቱ ብቻ የተጠቀሰ ሀገራት ሁኔታ እንደሚያሳየው፣ ለምርምር መከናወን መቻል ወይም አለመቻል ዋነኛው ምክንያት ይህ ነው፡፡ ነገር ግን፣ በዝርዝሩ ስማቸው ያልተጠቀሰው ሀገራት ያለመጠቀሱም እንደሚያሳየው ለሁኔታው ብቸኛ መንስኤ ተደራሽነት ብቻ አይደለም፡፡ ለምሳሌ የአፍጋኒስታን እና ሶማሊያን ሁኔታ ብንመለከት፣ ምርምር ለማካሄድ የሚሆን ደህንነት ለረዥም ጊዜ በሀገራቱ ያልነበር ቢሆንም፣ በተመሳሳይ መልኩ የረዥም ጊዜ ያለ መረጋጋት ከሚታይባት ከየመን በሁለት እጥፍ ተጠቅሰው እናያለን (የመን፣ 36፤ አፍጋኒስታን 60 እና ሶማሊያ 71)፡፡ የተደራሽነት እጦት እንደ ገደብ የተወሰነውን መልከዓ-ምድራዊ ቸልታ የሚገልጽ ሲሆን፣ እንደ ማመቻቻ መንገድ ደግሞ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ምርምር የተደረገባቸው ሀገራት ለምን በተመራማሪው ማኅበረሰብ ዘንድ ለምን ከፍ ያለ ትኩረት እንደ ተሰጣቸው ይገልጻል፡፡ ከአካላዊ ተደራሽነት በተጨማሪ፣ በምርምር እና ቲዎሪ ላይ ተመስርተው ወደ መልከዓ-ምድራዊ አካባቢዎች ማዘንበልም ይታያል፡፡ በሕንድ የተከናወነው ስርዓተ-ጾታ እና መደብ ኀልቶ

---

[a] Relatively new nations had very few references, but are not included.

[b] Including (in order of increasing reference): Cabo Verde, Curacao, Faeroe Islands, Northern Mariana Islands, American Samoa, Channel Islands, Isle of Man, Turks and Caicos, Aruba, French Polynesia, Palau, Marshall Islands, Bermuda, New Caledonia, Cayman Islands, St. Vincent and the Grenadines, Tuvalu, Antigua and Barbuda, Federated States of Micronesia, St. Kitts and Nevis, Sao Tome and Principe, Kiribati, Comoros, Solomon Islands, Vanuatu, Dominica, the Bahamas, St. Lucia, Malta, Grenada, Tonga, Seychelles and Cyprus.

[c] Including (in order of increasing reference): Turkmenistan, Kyrgyzstan, Azerbaijan, Belarus, Moldova, Estonia, Uzbekistan, Lithuania, Tajikistan, Latvia, Armenia, Kazakhstan, Ukraine and Georgia.

[d] Including (in order of increasing reference): Qatar, UAE, Bahrain, Kuwait and Oman, excluding Saudi Arabia.

የታየበት ምርምር፣ እንዲሁም በቸነፈር ላይ በኢትዮጵያ የተሠራው ሥራ ለዚህ በማሳያነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ በእነዚህ ሀገራት በቀጣይነት የተካሄዱ ምርምሮች እንዳሳዩትም እነዚህን ቀመሮች ጨምረው ለማጠናከር የሞከሩ ሲሆን፣ ይህም በቻምበርስ (2006) የተነሳውን ለጥናት ቅርብ በሆኑ 'ዝነኛ' ርዕሰ ጉዳዮች አማካኝነት የሚከሰትን አድልዎ ያጠናክራል፡፡

**የሕዝብ ብዛት**

በልማት ጥናት ምርምር በተደጋጋሚ ከተጠቀሱት 15 ሀገራት መካከል፣ 8ቱ ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት ያላቸው ሀገራት ናቸው፡፡ ምርምሮች ከፍተኛ ብዛት ባላቸው ሕዝቦች ላይ ተጽዕኖ ማምጣታቸው ስለማይቀር፣ እንዲሁም ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት ያላቸው ሀገራት ተያያዥ ከሆነው ከፍተኛ የምጣኔ ሀብት ጋር ተያይዞ ባላቸው ከፍተኛ መልከዓ-ምድራዊ ፖለቲካዊ ሚና ጭምር በእነዚህ ሀገራት ላይ ምርምር የማድረግ ፍላጎት መፈጠሩ የሚጠበቅ ነው (Hendrix, 2017)፡፡ በአንጻራዊነት በሕዝብ ብዛት የሚጠቀሱት ሀገራት ኬንያ፣ ጋና፣ ታንዛኒያ፣ ቺሊ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ፔሩ እና አርጀንቲና ቢሆኑም፣ በተደጋጋሚ የመጠቀሳቸውን ያህል የበዛ ሕዝብ የላቸውም (እንደ ኢትዮጵያ፣ ቬትናም፣ ግብጽ የመሳሰሉት ሀገራት በዝርዝሩ ያለ መካተታቸውን ልብ ይሏል)፡፡ እንደ ማውሪተስ ያሉ በአንጻራዊነት ዝቅተኛ የሕዝብ ብዛት ያላቸው ሀገራት ከብሩኔ አምስት እጥፍ በልጠው በተመራማሪዎች ተመርጠው ጥናት የሚካሄድባቸው መሆኑ፣ እንደ ተደራሽነት ሁሉ፣ የሕዝብ ብዛትም ነጥሎ የሚያነሳው ስፍራ እንዳለ እንመለከታለን፡፡ በሰምነር (2011) እንደ ተብራራው አብላጫዎቹ የዓለማችን ድሀ ሰዎች በእርግጥም ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት ውስጥ የሚኖሩ አይደሉም፡፡ የድህነት ቅነሳ ጥረቶች ድህነት በተጋረጠባቸው ሰዎች ላይ እንጂ ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት ላይ ማተኮር የማይኖርባቸው መሆኑ ላይ ከሰምነር ጋር እንስማማለን፡፡ ሆኖም፣ ይህ መከናወን ያለበት ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሀገራት በሚተዉበት ሁኔታ መሆን የለበትም፣ ምክንያቱም መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሀገራት ያሏቸው አቅርቦቶች ዜጎቻቸውን እንዲጠቅሙ የማድረግ የተሻለ ችሎታ እና ኃላፊነት አለባቸው፡፡

**ቋንቋ**

ቋንቋ የምርምር መልከዓ-ምድራዊ ስርጭት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራል፤ እጅግ በተደጋጋሚ ከተጠቀሱት 15 ሀገራት መካከል 7ቱ እንግሊዘኛ ከኦፊሴላዊ ቋንቋዎቻቸው መካከል አንዱ ሲሆን፣ የጥናት ውጤቶቹ የሚታተሙትም በዚሁ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ነው፡፡ አብላጫዎቹ ቀሪ ሀገራት ደግሞ ከዓለም እጅግ ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት የሚገኝባቸው ናቸው (ቻይና፣ ብራዚል፣ ሜክሲኮ፣ ኢንዶኔዥያ እና ባንግላዴሽ)፡፡ ነገር ግን፣ በአንጻራዊነት የእነዚህን ያህል ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት የሌላቸው፣ እንዲሁም ብሔራዊ ቋንቋቸው እንግሊዘኛ ያልሆነ እንደ ቺሊ እና ፔሩ ያሉ ሀገራት ተለይተው ይወጣሉ፡፡ የሕዝብ ቡድኖቹን አውጥተን፣ በተደጋጋሚ ያልተጠቀሱት ሀገራት እያንዳንዳቸው ከቤሊዝ በስተቀር እንግሊዘኛን በኦፊሴላዊ ቋንቋነት እንደማይጠቀሙት ለመመልከት እንችላለን፡፡ እጅግ ብዙ የሕዝብ ብዛት ኖሯቸው በተደጋጋሚ ካልተጠቀሱ ሀገራት መካከል፣ ምርምር እንዳይካሄድ የሚያግዱ ተደራራቢ ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ያሉባት ሰሜን ኮሪያ፣ ላለፈው ግማሽ ክፍለ ዘመን ያለ መረጋጋት የናጣት የመን ይገኙበታል፡፡ የቋንቋ ሁኔታ ለምን ድህረ-ሶቭየት ሀገራት፣ ከእነርሱም ውስጥ አንዳንዶቹ ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት ያላቸው እና በአንጻራዊነት መረጋጋት የሚታይባቸው (ለምሳሌ ዩክሬን እና ኡዝቤኪስታን) ለምን የተወሰነ ጥናት እና ምርምር ብቻ እንደ ተካሄደባቸው ይገልጻል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ፣ አምስት ወይም ስድስቱ የባህረ ሰላጤ ትብብር ምክር ቤት አባላት ሀገራት ያለመጠቀስ በቋንቋ እና በዝቅተኛ የሕዝብ ብዛት ሊገለጽ ይችላል፡፡ ነገር ግን፣ በእነዚህ ሀገራት የሚታየው ያልተጠበቀ ከፍተኛ የምጣኔ ሀብት እድገት እና የሰዎች ልማት ለማነጻጸር ያህል እንኳ ቢሆን፣ ለምን እንዳልተካተቱ እንድንጠይቅ ይጋብዛል፡፡

**ግንኙነቶች**

ቋንቋ፣ የሕዝብ ብዛት እና ተደራሽነት አንዳንዶቹን መልከዓ-ምድራዊ አካሄዶች ለመግለጽ የሚያግዙን ቢሆንም፣ በእነርሱ አማካኝነት ብቻ ሁኔታው ተገልጾ አያልቅም፡፡ ሌላው መንስኤ ደግሞ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ እና ግለሰባዊ ግንኙነቶች የሚጫወቱት ሚና ነው (Alesina and Dollar, 2000; Barro and Lee, 2005; Berthelemy, 2006; De Mesquita and Smith, 2009; Dollar and Levin, 2006; Hendrix, 2017)፡፡ ታሪካዊ እና ፖለቲካዊ ግንኙነቶች ስንል፣ የቅኝ ግዢ ትስስር፣ ፖለቲካዊ ትይይዝ፣ ወታደራዊ ወዳጅነት እንዲሁም የንግድ መዋዕለ ፈሰስ ማለታችን ነው፡፡ ለምሳሌ በአንዳንዱ ጊዜ የምርምር ማዕከላት የሚገኙባቸው ስፍራዎች ከቀድሞ የቅኝ ግዢ ጋር የተያያዘ እንደ ሆነ ለመመልከት እንችላለን፡፡ ግለሰባዊ ግንኙነቶች ስንል ደግሞ፣ አንዳድ ክልሎች የሚካተቱበት ወይም የሚተዉበት፣ እንዲሁም ለልማት ጥናት ሕትመቶች ጠቃሚ የሆነው፣ ያልሆነው እና አሳሳቢው ሁኔታ የሚተረጎምባቸው የግለሰባዊ ምርጫዎች ድምር ማለታችን ነው፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነን ከሕትመቱ ግብ እና ዓላማ ጋር አይሄዱም ተብሎ ስለሚታሰብ፣

የኢንተርናሽናል ዲቨሎፐመንት ፕላኒንግ ሪቪው ሕትመት ከቀድሞ ሶቭየት ሕብረት ሀገራት የተገኙ ሥራዎችን ለማተም ያለ መፈለጉ ነው (Hammett and Gough, 2016)።

**አሰላስሎት**

ይህ የሙግት ጽሑፍ በልማት ጥናት እና ምርምር ውስጥ መልከዓ ምድራዊ መድልዎ መኖሩን በተመለከተ አይደለም። ይህ ጉዳይ በእርግጥም የሚታወቅ ሲሆን፣ እነዚህ ልዩነቶች ቀጥለዋል (Barro and Lee, 2005; Berthelemy, 2006; De Mesquita and Smith, 2009; Dollar and Levin, 2006; Hendrix, 2017)። አንዳንዶቹን አስተዋጾ የሚያደርጉ ምክንያቶች ያወሳን ቢሆንም፣ መልከዓ-ምድራዊ ተካታችነት ወይም ያለመካተት ቅድሚያ የሰጠነው ጉዳይ አልነበረም። በአንጻሩ፣ እነዚህ ሁለት ነጥቦች ራሳችንን ከመልከዓ-ምድራዊ መድልኦዎች አንጻር በሚገባ እንድንፈትሽ እና ከጥና ዘርፉ እንዲሁም ከተማራማሪዎች ማኅበረሰብ ጋር በተገቢው መንገድ በመቆራኘት የምንሠራበትን መንገድ እንድንቀይር መሠረት የሚጥሉ ናቸው። ተመራማሪዎች 'አንድንም ሰው ያለ መተዉ'ን አጀንዳ ለመደገፍ እድሉ ያላቸው ሲሆን፣ ዘላቂ የልማት ግቦች ይህንን ዓላማ ከቅነሳ እና ከአዋጪነት ባለፈ እንዲያስፋፉ የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት ይችላሉ። ነገር ግን፣ የጋራ ድርጊታችን አንዳንዶችን ወደኋላ የሚያስቀርበትን መጠን መመዘን እና፣ ያለ መካተት እና የእውቀት ክፍተትን ለመሙላት አቅጣጫ እንዴት አድርገን መቀየር እንዳለብን መፈተሽን ይጠይቃል።

ቻምበርስ (2006) እንደሚሟገተው በዘርፋችን ያሉ አንዳድ መድልኦዎች፣ ይበልጡን ከ'መስኩ' የሚገኙ የትርክት ገለባዎች ከመሆናቸው የተነሳ ለትምህርታዊ ጥናት የሚያመቹ ስላይደሉ፣ ይህ ራስን የመፈተሽ ጥሪ እጅግ ጠቃሚ እንደ ሆነ እናምናለን። ስለዚህ፣ የልማት ጥናት ተፈጥሮ እና 'የታቀደ የመስክ ጉብኝት' ላይ ግላዊ አሰላስሎትን ማካሄድ፣ በዘርፋችን የሚከሰተውን መልከዓ-ምድራዊ ያለማካተት ለመገደብ የሚያችለውን እሳቤ ሊያስገኝልን ይችላል። ከዚያም በላይ፣ የዓለም ሕዝብ ወደ ከተሜነት በሚያደርገው የጥድፊያ ሩጫ ውስጥ የሚካሄዱ 'አጭር ጊዜ የከተማ ጉብኝቶች' ላይ መድልኦዎች የራሳቸውን ተጽዕኖ ማሳረፋቸው የማይቀር ሲሆን፣ ድህነትን በከተማ እንዲሁም በገጠር መቼት ውስጥ በተጋፈጡት ላይ የተሳሳተ መረጃ እና በቅጡ ያልተገናዘቡ እውነታዎች እንዲሰራጩ ያደርጋል (Chambers, 2006, p. 13)።

ተደራሽነት፣ የሕዝብ ብዛት፣ ቋንቋ እና ግንኙነቶች ምርምር የሚካሄድባቸውን እና የማይካሄድባቸውን ስፍራዎች መወሰን ላይ ቁልፍ ምክንያቶች ሆነው አግኝተናቸዋል። ነገር ግን፣ ይህ ገና እጅግ ጠቃሚ የሆነ ውይይት ጅማሬ ብቻ ነው። እነዚህን አካሄዶ ስናሰላ፣ መልከዓ-ምድራዊ ያለ መካተት እና መተዉ የሚያስከትሉና ሉላዊ ኢ-እኩልነት እና አሉታዊ ተጽዕኖን እጅግ ተጋላጭ በሆኑ እና ለመቋቋም አቅሙ በሌላቸው ሕዝቦች ላይ እንዲከሰቱ የሚያደርጉ ሂደቶችን ለማስወገድ መጣር ይኖርብናል። የጋራ ምርምሮቻችን ፈትሸን በዘላቂ የልማት ግቦች ውስጥ ለተዘረዘሩት ግቦች - የልማት ምርምር እና ምርምር እና ትግበራ በተዋረድ ከቀጠለ ልናሳካቸው የማንችላቸውን ግቦች እውን ለማድረግ - መከናወን የ2030 አጀንዳዎች እና ዘላቂ የልማት ግቦች መልካም ዕድል አቅርበውልናል። ለመጪው አስር ዓመት እና ኢጋማሽ ዘላቂ የልማት ግቦች የቀዳሚ ጉዳዮች፣ የገንዘብ አቅርቦት እና ትኩረት የሚሰጥባቸውን ሁኔታዎች የሚወስኑ ሲሆን፣ በቃላቱ ውስጥ የተነሳው የተደራሽነት ጉዳይ ሁለቱንም የልማት ትግበራ እና ምርምሮች፣ እነዚህን ብርቱተ መሻት ያለባቸው ግቦች ማስፈጸም ልዕለ-ለውጥ የሚያስፈልገው መሆኑን እንድናሰላስል ሊያበረታቱን ያስፈልጋል።

በዚህ መልኩ ሲቀመጥጥ መልከዓ-ምድራዊ ያለ መካተት የጥናት ዘርፉ አሳሳቢ ጉዳይ ከመሆን ይልቅ እንደ እድል ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል። ምርምራችን ውሳኔ ሰጪዎችን እንደሚደግፍ እና ተገቢውን ድጋፍ እንደሚያደርግ ለማረጋገጥ ጊዜን ይሰጠናል። የጋራ ምርጫዎቻችን ለአካታችነት እና ተደራሽነት ግብ አስተዋጾ ማድረግ ያለባቸው ጊዜ አሁን ነው። እናም፣ ያለውን አካሄድ በድጋሚ ለማሰላሰል እና ለተማራማሪዎች የእውቀት ክፍተት የቱጋ እንዳለ በማሳየት ምሪትን ለመስጠት፣ እነዚያን ክፍተቶች ለመሙላት አዳዲስ ምርምሮች የሚካሄዱበትን ምክንያት እና መነሳሳት ለማቀበል ጊዜው ነው። ከሀመት እና ጋዉ (2016) ጋር በመስማማት፣ ዘላቂ የልማት ግቦችን ለልማት ጥናት ተመራማሪዎ (እንዲሁም ለአርትኦት ሰሪዎች እና ሕትመቶች) ያላቸውን ማዕከል እና አስተዋጾ ሳይተዉ፣ ካለፈ የእሳቤ ገደብ እና መልከዓ-ምድራዊ መድልዎ ነጻ እንዲወጡ የሚያስችል እድል እንዳቀረቡልን እናስባለን። እነዚህን ክፍተቶች ከመሙላት ምሳሌዎች አንዱ አዳዲስ ተመራማሪዎች ስለ ክፍተቶቹ ተገቢው መረጃ እንዲኖራቸው ማድረግ እና ለእውቀት ተጨማሪ አስተዋጾ እንዲያደርጉ ማነሳሳት ይጠቀሳል። ሌሎች ጉዳዮች ደግሞ ልዩ ልዩ መልከዓ-ምድራዊ ሁኔታዎችን ይጨምራሉ። ልዕለ-ለውጡ

ሊካሄድ የሚችልበትን መንገድ በተመለከተ መልስ ለመስጠት የማንችል ቢሆንም፣ በልማት ጥናት ምርምሩ ማኅበረሰብ ላይ የተጣለውን ኃላፊነት ለመወጣት በሚያስችልና ማንንም ወደ ኋላ ላለመተዉ በሚያስችል መንገድ የአስተሳሰብ አመራር እና ማስረጃን በሚያስገኝ መልኩ ፈጠራ እና አዲስ ሀሳብ አፍላቂነትን የሚያነቃቃ ውይይት እንዲነሳ እንፈልጋለን፡፡

**የአቅራቢዎቹ ማስታወሻ**


ዶክተር ሎጋን ኮክሬን በካርልተን ዩኒቨርስቲ የባንቲንግ ፌሎ አካል ነው፡፡

ዶክተር አሌክ ቶርንቶን በዩ.ኤን.ኤስ.ደብሊው ካንቤራ አውስትራሊያ፣ በስኩል ኦቭ ፊዚካል ኢንቫይሮመንት ኤንድ ማቲማቲካል ሳይንስስ ባለ ብዙ ልምድ አስተማሪ ነው፡፡ በተጨማሪም በደቡብ አፍሪካው የጆሀንስበርግ ዩኒቨርስቲ የስኩል ኦቭ ቱሪዝም ኤንድ ሆስፒታሊቲ፣ የማኔጅመንት ፋኩልቲ የምርምር አካል ነው፡፡ በምርምር ሕይወቱ በዘላቂ የከተማ ልማት እና የከተማ የምግብ አስተዳደር የወሳኝ ቀመሮች አቀራረብን ይከተላል፡፡

## ORCID

Alec Thornton http://orcid.org/0000-0001-6562-535X


**ማጣቀሻዎች**


Alesina, A. and D. Dollar, 2000, ‘Who gives foreign aid to whom and why?’, Journal of Economic Growth, Vol. 5, pp. 33–63.

Barro, R. J. and J.-W. Lee, 2005, ‘IMF programs: Who is chosen and what are the effects?’, Journal of Monetary Economics, Vol. 52, No. 7, pp. 1245–1269.

Berthelemy, J.-C, 2006, ‘Bilateral donors’ interest vs. recipients’ development motives in aid allocation: Do all donors behave the same?’, Review of Development Economics, Vol. 10, No. 2, pp. 179–194.

Bigsten, A., 2017, ‘Development research for global justice’, Forum for Development Studies, Vol. 44, No. 1, pp. 133–139.

Boas, M., 2017, ‘Fragile states as the new development agenda?’, Forum for Development Studies, Vol. 44, No. 1, pp. 149–154.

CARIAA, 2016, ‘Consortia’, http://cariaa.net/.

CDKN, 2016, ‘Regions’, http://cdkn.org/regions/africa/?loclang=en_gb#.

Chambers, R., 1981, ‘Rural poverty unperceived: Problems and remedies’, World Development, Vol. 9, No. 1, pp. 1–19.

Chambers, R., 2006, Poverty Unperceived: Traps, Biases and Agenda, Working paper series, 270, Brighton: IDS.

Cochrane, L. and A. Thornton, 2016, ‘Charity rankings: Delivering development or de-humanizing aid?’, Journal of International Development, Vol. 28, pp. 57–73.

De Mesquita, B. B. and A. Smith, 2009, ‘A political economy of aid’, International Organization, Vol. 63, pp. 309–340.

Dollar, D. and V. Levin, 2006, ‘The increasing selectivity of foreign aid, 1984–2003’, World Development, Vol. 34, No. 12, pp. 2034–2046.

Eyben, R., Guijt, I., Shutt, C. and Roche, C., eds, 2015, The Politics of Evidence and Results in International Development: Playing the Game to Change the Rules?, Bourton on Dunsmore: Practical Action Publishing.

Hak, T., S. Janouskova and B. Moldan, 2016, ‘Sustainable development goals: A need for more relevant indicators’, Ecological Indicators, Vol. 60, pp. 565–573.

Hammett, D. and K. V. Gough, 2016, ‘IDPR in 2016 and beyond’, International Development Planning Review, Vol. 38, No. 4, pp. 347–357.

Hendrix, C. S., 2017, ‘The streetlight effect in climate change research on Africa’, Global Environmental Change, Vol. 43, pp. 137–147.

ICSU and ISSC, 2015, Review of the Sustainable Development Goals: The Science Perspective, Paris: International Council for Science.



Jerven, M., 2017, ‘How much will a data revolution in development cost?’, Forum for Development Studies, Vol. 44, No. 1, pp. 31–50.

Scholte, J. A. and F. Soderbaum, 2017, ‘A changing global development agenda?’, Forum for Development Studies, Vol. 44, No. 1, pp. 1–12.

Sumner, A., 2011, The New Bottom Billion: What if Most of the World’s Poor Live in Middle

Income Countries, Washington, DC: Center for Global Development.
UN, 2016, ‘LeavingNoOne Behind’, http://unstats.un.org/sdgs/report/2016/leaving-no-one-behind.
UN SDSN, 2015, Indicators and a Monitoring Framework for the Sustainable Development Goals: Launching a Data Revolution for the SDGs, New York, NY: United Nations Sustainable Development Solutions Network.
UNDP, 2016, ‘Helen Clark: Speech on “A Commitment to Leave No One Behind: Equity in the SDGs”’, www.undp.org/content/undp/en/home/presscenter/speeches/2016/06/04/helen-clark-leave-no-one-behind-equity-in-the-sdgs-save-the-children-annual-meeting.html.